ስብዕና እና ተቋማዊ ባህሪን

የመገንባት ሃላፊነት

በአብክመ ስነ-ምግባርና

ፀረ-ሙስና ኮሚሽን ጎ/ቅ/ፅ/ቤት የተዘጋጀ

ታህሳስ/2015 ዓ.ም

ጎንደር

የሰልጠናው ይዘት፡-

1. ስብዕና (Personality) ምንድነው?
2. 5ቱ የስብዕና ወሰኖች/መለኪያዎች/The Big 5 Dimensions of personality/
3. ተቋማዊ ባህሪ/ Organizational Behavior/
4. ተቋማዊ ቁርጠኝነት/ዝግጁነት/

የስልጠናው ዋና ዓላማ፡-

- የመልካም ስብዕና መሳኝነትን በመረዳት ተቋማዊ ያደርጋሉ።

ዝርዝር ዓላማዎች፡-

- ስብዕና በየጊዜው እየዳበረ የሚሄድና ለስኬት ቁልፍ መሆኑን ይገነዘባሉ፤
- ተቋማዊ ቁርጠኝነት የሚመጣው በትክክል የተቋሙን ባህሪ ስንገነዘብ መሆኑን ያሳያሉ፤
- ውጤታማ ተግባር በመከወን የህዝብን ትኩረት መሳብ እንደሚቻል ይገልፃሉ።


መግቢያ

- ይህ ስልጠና የተዘጋጀው ራስን ወደ ውሥጥ በመመልከት/inward looking/ለተሻለ አፈፃፀም የሚያበቃ የውስጥ አቅማችን እንድንቃኝ ለማመላከት ታስቦ የተዘጋጀ ነው።
- ምንም እንኳ የተለያዩ ንድፈ-ሃሳቦች የተካተቱበት ቢሆንም ተግባር ተኮር ለማድረግ ከተጨባጩ እውነት ጋር በማስተሳሰር ራሳችንንና አካባቢያችንን ለውጤታማ መስተጋብር እንድናይ ፍንጭ ይሰጣል።

ራስዎን ይጠይቁ!

- እኔ ማነኝ?
- ተግባርና ሃላፊነቴን ለመወጣት ምን ያህል ቁርጠኛ ነኝ?
- ስብዕናየስ እንዴት ይገለፃል?




How your brain, genes, and body work together to make you YOU
Who am I?
Richard Walker

1.ስብዕና (Personality) ምንድነው?

- ስብዕና ማለት በአንፃራዊነት ቋሚ የሆነ የስሜት፣የሃሳብና የባህሪ ስብስብ ሲሆን የአንድ ግለሰብ ልዩ መገለጫ ነው።።
- በተለያዩ ሁኔታዎች፣ጊዜያትና ቦታዎች ግለሰቦች የሚያሳዩዋቸው ወጥ ባህሪያት፣ ግንዛቤዎችንና አሳቤዎችን የሚገልፅ ነው።።

- ስብዕናችን ከምነው የሚመጣው? የተለያዩ አሳቤዎች/school of thoughts/ እንደሚገልፁት ስብዕናችን የሚመሰረተው ከሁለት ዋና መሰረታዊ አካላት ነው። እነሱም፦

  - በተፈጥሮ ከወላጆቻችን የምንወርሰው /Inherited characteristics i.e. nature/
  - ከአካባቢው የምንማረው/learned characteristics i.e. nurture/


Physical Characteristics
Heredity
Brain
Religion
Culture
Social Experiences

- ይህ ጥምረት ነው የእኛን የመሆን ብይን እና የአሠራር መንገዳችን የሚወስነው ነው።።
- በአጠቃላይ ከአከባቢው ጋር ውጤታማ በሆነ መልኩ ሁለንተናዊውን መስተጋብር በማዛመድ ተስማሚ ያደርጋል።

ስብዕና በምን ይገለፃል?

- ካራክተር **የስብዕና** ዋነኛው አሰኳል ነው። ካራክተር ማለት የስነ-ምግባር፣ፀባይና ባህሪ ድምር ነው።
- በችሎታ፤በብቃት ከፍታ ላይ መውጣት ቢቻልም ከፍታው ላይ የሚቆየው መልካም ስብዕና ካለ ነው። ከሌለ ግን ወድቆ መፈጥፈጥ አለ።

- ሰብዕናችን ከሌላው የምንለይበት ከመልክና ከቁመና በተጨማሪ የማንነታችን መታወቂያ ነው።
- ጠንካራ ሰብዕና የሕይወትን ጎዳና በግልፅ የማሳየት እና አካሄዱን ሳይሸሽ የመከተል ችሎታ አለው።
- ስለዚህ እንደግለሰብ ሰዕብና ላይ መሰራት ለስኬታማ መስተጋብር/ህይዎት/ አይነተኛ መሳሪያ ነው።

❖ ስብዕና/Personality/ የ3 ክፍሎች ወይም አካላት ጥምረት/ ድምር/ ውጤት መገለጫ ነው እነዚህም፡-

- ስሜት/Feelings/
- የመገንዘብ አቅም/Cognition/ እና
- ባህሪ/Behavior/ ናቸው።

- ስሜት/Feelings/-ደስታ፣ብስጭት፣ንዴት፣ ሳቅና ቁጣ የሚገለፁበት የስብዕናችን ክፍል ነው።
- የመገንዘብ ብቃት /Cognition/- እውቀት፣አስተሳሰብ፣አመለካከት/attitude/፣የሃሳብ ፍሰት/thought flow/፣የሃሳብይዘት/thought content/ የሚባለው ነው።

ባህሪ/Behavior/

አለባበሳችን፣አነጋገራችን፣አመጋገባችንና አኗኗራችን ነው።

- ስብዕና የእነዚህ የ3ቱ ድምር ውጤት ሲሆን በማንኛውም ጊዜ የሚበለፅግ ነው።



1.1. 5ቱ የስብዕና መሰኖች/መለኪያዎች/The Big 5 Dimensions of personality/

- በእነዚህ መለኪያዎች መሰረት ስብዕናችን ከፍ ወይም ዝቅ አለያም መካከለኛ ሊሆን ይችላል። የአንድን ሰው ስብዕና የምንለካበት 5ቱ መሰረታዊ ባህሪያት /The most fundamental traits of personality/ የሚባሉት የሚከተሉት ናቸው፦

- የተረጋጋ ስሜት/Neuroticism or Emotional stability/
- ስሙምነት/Agreeableness/
- ሃሳብን/ስሜትን/ መግለፅ/Extraversion/
- ራስን መግዛት/Conscientiousness/ እና
- ለልምድ ራስን ክፍት ማድረግ/openness to experience/ ናቸው።


Openness
Neuroticism
Conscientiousness
Personality
Agreeableness
Extraversion

1.1.1.የተረጋጋ ስሜት/Emotional-stability/

- በውጥረት ጊዜ ስሜትን ሚዛናዊ በሆነ ሁኔታ የማስጠበቅ አቅም ወይም ብቃት ነው/the capacity to maintain ones emotional balance under stressful circumstances./።

- አንዳንድ ሰው አሁን ደስተኛ ነው፤ አሁን ይናደዳል። በሚደሰትበትና በሚናደድበት ጊዜ በአዕምሮው ውስጥ ስዊንግ የሚያደርግበት ከሰፋ bipolar disorder ይባላል::
- ስሜናደድ ያዝ ቻል የምናደርግ ስንደሰትም በልኩ ማስተናገድ መቻል ነው።
- የተረጋጋ ስሜት/emotional stability/ የጥሩ ስብዕና ማሳያ/መገለጫ/ ነው።

1.1.2. ስሙምነት/Agreeableness/

- ከራስ ፍላጎት በፊት የሌሎችን የማስቀደም ችሎታ ነው/ a person's ability to put others needs before their own/.
- የሰዎችን ችግር እንደራስ በማየትና መፍትሄ በመፈለግ እገዛ ከሚፈልጉ ሌሎች ሰዎች ጋር ተባብሮ መስራት የጠንካራ ስብዕና ልዩ ማሳያ ነው።። .

⊕ ምን ያህል ተስማምታችሁ ከሰዎች ጋር መስራት ትችላላችሁ?

- እንዴት ነው ስራ ቦታ ያሉ ባልደረቦቻችሁ ይወዳችኋል? ስራ ላይ ተባባሪ ናችሁ? ወይስ የምን አገባኝ ደንበር አለችሁ?

- የተሻለ ሃሳብ ይዞ የመጣን በመቀበል የእናንተን ሃሳብ ትተዋለች?

- ስምሙ ከሆን ከስራችን ውጤታማነት በተጨማሪ ለሰዎች የምንመች እምነት የሚጣልብን እንሆናለን ማለት ነው።

- **የማይሆንን ነገር በግልፅ አይሆንም** ማለት መልመድና ባህል ማድረግ እንዳለብን የሚገልፅ ነው/ **assertiveness**/ ።
- የግል ድንበሮችን ማዘጋጀት ይማሩ! አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ **“አይ”** ለማለት ይድፈሩ፤ እራስዎን ለመከላከል ይማሩ ፣ በሌላ አነጋገር በብቃት መጋጨት ይማሩ ።
- አንዳንዴ ብግን ብለን አንናገረውም ውስጣችን ይቆስላል ይጠራቀማል፤ ጨዋ ሆነን መጥተን በዚህ ጉዳይ አዝኛለሁ ብለን አንገልፅም በውስጣችን ነው የምንይዘው።

- ለራሱ መብትና ነፃነት፣ለህዝቡ ክብርና ፍቅር፣ለሀገሩ ሰላምና ደህንነት የማይሟገት ዜጋ በቁጥር እበዛ ሲሄድ አገር ትሞታለች።
- መሆን የማይገባን ነገር መሞገት ተገቢ ነው፤ ሰዋዊ ነው፤ሞራላዊና ስነ-ምግባራዊ ነው።
- ዝም ማለት በማይገባ ጊዜ ዝም ማለት በራሱ ሙስና ነው።

1.1.4. ለልምድ ራስን ክፍት ማድረግ/openness to experience/

- ነገሮችን ለመልመድ ራስን ክፍት ማድረግ ነው።
- የዕይታ አድማሳችንን ማስፋት፣ከተለመደው አካሄድ መለቀቅ በአዲስ መንገድ ለማሰብና ለመስራት መሞከር ነው።
- ዕድሜ ምንም ይሁን ምን ለመማር መፍራት የለብንም ።

- በሙያ ውስጥ እራስን ማሻሻል፣ ብቃትን በየጊዜው በማሻሻል በተቻለ መጠን አዲስ ነገር መማር፣ሁል ጊዜም ዘመናዊ የመረጃ ፍሰትን ለመቀበል ዝግጁ መሆን።
- የተሟላ ስብዕና ለመመስረት ከፍተኛ ዕውቀት እና ተለዋዋጭ አስተሳሰብ አስፈላጊ ሁኔታዎች ናቸው።

- ማህበራዊ ክበብዎን ያስፋፉ ፣ አዲስ ሰዎችን ይተዋወቁ ፣ የሌላውን ሰው ተሞክሮ ይቀበሉ ፣ ራስዎን መሆንዎን አይርሱ።።
- በምላሹም ሞቅ ያለ ችሎታዎን ለሌሎች ለማካፈል እና እርዳታ ለመስጠት አያመንቱ ።።

- ዓለማ-መር፤ራስን የሚቆጣጠር፤ሃሳበ ሙሉ፤ጠንካራና ሃላፊነት የሚሰማው ስብዕና ስለሆነ ለስኬት ዋና ቁልፍ/ቅመም/ ነው።።
- ራሱን በከፍተኛ ዲሲፕሊን የሚመራ፤ እያንዳንዱ የሚያደርጋቸው መስተጋብሮች ቀጣይነት ባለቸው እቅዶች የሚያከናውን ሰው ስብዕና ነው።።

- የሙሉ ሰብዕና ባለቤት ለመሆን እና ለመቀጠል በራስ ላይ ዘወትር መሥራት ያስፈልጋል ።
- ሰብዕና ሁሌም ስለሚገነባ፤ሰብዕናን መፍጠር ማለቂያ በሌለቸው አጋጣሚዎች ውቅያኖስ ውስጥ ለራሱ ማለቂያ የሌለው ፍለጋ ነው።። በንቃት ፣ ለራስ ትኩረት በመስጠት እና ሀይወትን በፈጠራና በአዳዲስ እሳቤዎች በማጀብ ራስን ማግኘት ነው።

1.2.የጥሩ ስብዕና ባለቤት/owner of high quality personality/ ስንሆን ዕለት በዕለት በምናደርገው መስተጋብር እኛነታችን የሚያሳዩን መስታዎቶች፡-

❖ትዕግስት/Patience/-ጥሩ ስብዕና ሲኖራችሁ ትዕግስተኛ ትሆናላችሁ፡፡ ራሱን የሚገዛ ከተማን ከሚገዛ ይበልጣል ይባላል፡፡

- **ከችግር ፈጥኖ ማገገም/Resilient/-** ትወድቃለህ ግን ትነሳለህ፤ታጣለህ ግን ታገኛለህ፤ይህ ስብዕና ያለው ሰው ድንገት ይከሰራል ግን ያገኛል፤ይወድቃል ፣ ግን ይነሳል።

- ከችግር ፈጥኖ የሚያገግገሙ ሰዎች እጁን ዘርግቶ የሚያነሳቸው የለም፤ ግን ራሳቸው ራሳቸውን አይዞህ ብለው ያነሳሉ።

- **ፅናት/Persistence/-**

- ችግር ይመጣል ይቋቋሙታል፤ደጋግሞ ይመጣል ግን ይቋቋሙታል በዚህ መሃል ስብዕና ይገነባል።

- **ትህትና/Humility/-** ፍሬ ያለው ዛፍ ከቅርንጫፎቹ ዝቅ ይላል። ፍሬያችሁ ሲበዛ ትሁት ትሆናላችሁ ትህትና አያከስራችሁም ራሱን ዝቅ ያደረገ ከፍ ይላል። ትህትና **የግብዝነት ሕይወትን** በማስወገድ በንግግር እና በድርጊት ራስን ሆኖ መገኘት ነው።
- **የመርህ ሰው መሆን/Integrity/-** የትም ቦታ ሁን የመርህ ሰው ከሆንክ የምታሳየው ባህሪና ድርጊት ተመሳሳይ ነው የሚሆነው። የሰዎችን ፊትና የሃላፊነት ደረጃ እያየን የህግን ሚዛናዊነት የማናናጥብበት ማለት ነው።
- የማውቀው ሰው አለ ወይም የለም ሳትል በወጥነት የምታሳየው ባህሪ ነው።


❖ክብር የማይቀንስ /Honorable/-

- ❖ክብር የሁሉም መልካም ነገሮች ወይም ፀጋዎች ምንጭ ነው ይባላል።
- ❖የማይሆን ቦታ አልገኝም፣የለኔ-ምግባር ዝቅጠት እኔን አይገልፀኝም የማለትና ሆኖ መገኘት ነው። ማንም የቤተሰቤ አካል በድርጊቴ ከሚያፍርብኝ በክብር ኖሬ እንዲከብርብኝ አደርጋለሁ የማለት ነው።
- ❖ለራስና ሌሎች ክብር መስጠት የክብር ባለቤት ያደርጋል።



Respect is the more important element of personality.
It is like an investment. Whatever you give to others it will return you with Profit.


- **Type A-** መወዳደር የሚወዱ፤በብዙ ፕሮጀክት ስኬታማ መሆን ይሻሉ፤ተወዳድረው የግድ ማሸነፍ መሄድ አለባቸው ካለሸነፉ ድብርት ውስጥ ይወድቃሉ።ስራ ሲሰሩ በጭንቀት ውስጥ ሆነው ነው እንዲሁም ጠባቂና ብስጩ ናቸው።
- **Type B-** ስራ ሲሰሩ የተዝናኑ ናቸው፤ትዕግስተኛ ናቸው፤ሌሎች ያስቀመጡትን የጊዜ ገደብ አይወዱም በራሳቸው እርምጃ ልክ ነው መስራት የሚፈልጉት።


Type A
Type B
• Competitive
• Time Urgent
• Hostile and aggressive
• Relaxed
• Patient
• Easy going

- **Type C-** በጣም ጠንካራ ሰራተኞች ናቸው፣ጥርት አደርገው መስራት የሚፈልጉ ናቸው፣ጥልቅ አሳቢ ፣ስሜታዊ፣ጠንቃቃና ስልታዊ ና



- **Type D-** ሁሉን ነገር በአሉታዊ የሚያዩ ናቸው፣ጨለምተኛ ናቸው፣የመገለል ፍርሃት፣በራስ መተማመን የላቸውም፣ተስፋቢስ ናቸው.....።



የስብዕና መቃወስ/Personality disorder/ አይነቶች፡-

- ፀረ-ማህበራዊ የስብዕና መቃዎስ/Anti social personality disorder/
- ራስ ወዳድነት/Narcissistic/
- የሁሉንም ትኩረት የሚሻ የስብዕና መታወክ/Histrionic personality disorder/
- ከሰው የማያስቀርብ /Schizoids/

- ጥሩ ድርጊትን በቅንነት የማይቀበል የስብዕና መቃወስ/Obsessive compulsive disorder/
- በራሱ ውሳኔ መስጠት የማይችል/Dependent personality disorder/
- ተጠራጣሪ/Paranoid personality disorder/
- መሸሽ/Avoidant personality disorder/

....ወዘተ ናቸው።

- ማንኛውም ተቋም ሲመሰረት የራሱ የሆነ መነሻና መዳረሻ ሊሆን የሚችል ችግርና ዓለማን አንግቦ ነው።

- ተቋማዊ ባህሪ ማለት በተቋሙ ውስጥ ያሉ ግለሰባዊና ቡድናዊ የሆኑ ሰብዓዊ ባህሪን በመረዳት፣በመተንበይና በማስተዳደር የሚገለፅ ሲሆን ባለድሻ አካላትንም የሚያካትሊሆን ይችላል።

- በዚህ ሂደት ውስጥ ሌሎችን በአግባቡ መረዳትና ሌሎችም ራስን እንዲረዱ ማድረግ በጣም አስፈላጊ ነው።።
- ጤናማ የስራ አካባቢን ለማስጠበቅ አካባቢን መለመድና ልናሳካው ያቀድነውን ግብ በሚጠበቀው ልክ መረዳት ተገቢ ነው።።

- ልናሳካው የምንታተርለትን ተልዕኮ፣ ራዕይና ስትራቴጂ ለራስ አስርዖ መያዝና ግለቱን ጠብቆ ለውጤት ማብቃት ነው።
- ይህን እውን ለማድረግ እንደ ተቋም ሊያግባባ የሚችል ስነ-ምግራዊ ቋንቋ ያስፈልጋል። ይህ የሚሆነው በቀላሉ የተቋማዊ ባህሪን አስፈላጊነት ስንረዳ ነው።

- ፍትህ የህግ ስርዓቱ መሰረት ነው ይባላልና የምናሳያቸውና የምንተገብራቸው ስነ-ምግባራዊ ባህርያት ከተቋሙ ባህርይና ተግባር ጋር የተዋሃዱ መሆን አለባቸው።
- እኔ የተቋሜ ነፀብራቅ ነኝ፤ ተቋሜም እኔን ይመስላል በማለት ሙያዊ ተአማኒነታችንን እና አለኝታነትን ልንገልፀ ይገባል።

- የማንኛውም ተቋም ባህሪው ወይም ስነ-ምግባራዊ መርሆዎች መነሻቸው ማህበራዊ ዕሴቶች ናቸው። ተቋሙ የህግ የበላይነት እንዲከበር ይሰራል እንዲሁም ማህበረሰቡ ለትክክለኛ ፍትህ መስፈን የሚሰጠው አመኔታ የላቀ መሆኑ እንደ ማሳያ ይጠቀሳል።
- በዚህም የተቋሙ ውስጣዊና ውጫዊ ግንኙነት የሚገነባበትና የሚጠናከርበት ይሆናል።

- ባለንበት በ21ኛው ክ/ዘመን ከተቋማዊ ባህሪ አንፃር የስነ-ምግባርና እሴት ስርዓት መዘርጋት **በማንኛውም ተቋም ቅድሚያ የሚሰጠው ወሳኝ ሁነት** ነው። የፍትህ ተቋማት ደግሞ ለዚህ ፋና ወጊዎች ናቸው ተብሎ ይታመናል።
- ለዚህም ይረዳ ዘንድ ተቋማት ቀጣይነት ያለው ውጤት እንዲያስመዘግቡ በምሁራን በኩል የተለያዩ የተቋማዊ ባህሪ ንድፈ ሃሳቦች/እሳቤዎች/ ተራምደዋል።

2.1.የተቋማዊ ባህሪ ንድፈ ሃሳቦች

- ተቋማዊ ባህሪን በተመለከተ የተለያዩ ምሁራን የተለያየ ሃሳብ ቢያራምዱም፤ ጠቅለል ተደርጎ ሲታይ በዋነኝነት በተቋማዊ ባህሪ ዙሪያ የሚያጠነጥኑ አራት ንድፈ ሃሳቦች አሉ፡፡ እነሱም፡-

  ፩ የሰው ሃይል ንድፈ ሃሳብ

  ፪ የሁኔታ ንድፈ ሃሳብ

  ፫ የምርታማነት ንድፈ ሃሳብና

  ፬ የስርዓት ንድፈ ሃሳብ ናቸው፡፡

፩ የሰው ሃይል ንድፈ ሃሳብ /A human resource approach/

- ይህ ንድፈ ሃሳብ ትኩረት የሚያደርገው በሰራተኞች እድገትና ልማት ላይ ሲሆን በዚህም ብቃታቸው፣ፈጠራና አፈፃፀማቸው ከፍ እንዲል በማድረግ ላይ አፅንዖት ይሰጣል።

- ምክንያቱም የማንኛውም ተቋም ዋና ሃብቱና አንቃሳቃሽ ሞተሩ ሰራተኞች ስለሆኑ በማለት ይገልፃል።
- ተቋምን ተቋም የሚያደርጉት፤ **ተቋሙ የተቋቋመበት ዓለማ ውጤታማ** እንዲሆን የሚከውኑት በዋነኛነት ሰራተኞቹ ናቸው።
- በዚህ ንድፈ ሃሳብ መሰረት የፍትህ መምሪያን ህዝብ የሚመካበት የፍትህ ተቋም ከማድረግ አንፃር ምን ላይ ነን?

፪ የሁኔታ ንድፈ ሃሳብ/A contingency/ situational/ Approach/

❖ለሁሉም ሁኔታዎች አንድ ምርጥ መንገድ አለ ከሚለው ከባህላዊው ንድፈ ሃሳብ ይልቅ የተለያዩ ሁኔታዎች የተለያዩ ተግባራዊ ባህርያትን ይፈልጋሉ የሚለው ውጤታማ ያደርጋል።

- ወደ ተግባር ከመግባታችን በፊት እያንዳንዱን ሁኔታ ቅድሚያ ሰጥተን እንድንተነትን /situational analysis/ያበረታታናል።
- በዚህም ያስቀመጥነው ዓላማ ውጤታማ ሆኖ የማህበረሰቡን ትኩረት በሚጠበቀው መልኩ ለመሳብ ይረዳ ዘንድ ከነበረው ችግር ጋር ተላምዶ የነበረውን ወይም የቆውን ችግር ይዞ መቀጠል ሳይሆን ለጋጠመ ችግር ተገቢ

- መፍትሄ በማስቀመጥ ከጊዜው ጋር መራመድን ይጠይቃል፤ ብዙ ጊዜ ተቋሜ ወይም የምሰራው ስራ ማህበረሰባዊ ተቀባይነቱ ምን ያህል ነው? ምንስ ጠንካራና ደካማ ጎኖች አሉት? ....ወዘተ ብሎ ክፍተቶችን በመለየት በምን መልኩ ማጥበብ እንደሚቻል መተንተን ያሻል።

- በባለፈው በጀት ዓመት ውጤታማ ያልሆነበትንና አላሰራ ያለውን ችግር በአዲሱ በጀት ዓመትም አዝሎ የሚሄድ በርካታ አካል አለ።
- ለምሳሌ የሙሰና የወንጀል ድርጊት ለምንድነው ከዓመት ዓመት የጨመረ የሀግ ክፍተት ስላለ? ወይስ ህጉ በተገቢው መንገድ ስላልተተረጎመ?
- ችግሮችን ነቅሶና ነክሶ በመያዝ ያለውን ተሰጥዖ ለህዝብ በማበርከት ዘለቂ መፍትሄ ማስቀመጥ የብቁ መሪና ባለሙያ መገለጫ ነው።
- እኔ ከየትኛው ጎራ ነኝ? በማለት ራሳችን እንጠይቅ

የምርታማነት ንድፈ ሃሳብ/A Productivity Approach/

- ይህ ንድፈ ሃሳብ የግብዓት አሃድን ከውጤት አሃድ ጋር ሬሾ በመስራት ምርታማነትን የሚያነፃፅር ነው።
- የግብዓትና የምርት ንፅፅር የሚለካውም ከምጣኔ ሃብታዊ አንፃር ነው።
- ነገር ግን ከምጣኔ ሃብታዊ ጠቀሜታ አንፃር ከግብዓትና ምርት በተጨማሪ ሰብዓዊና ማህበራዊ ሚናዎችም አሉበት።

የሰርዓት ንድፈ ሃሳብ/A Systems Approach/

- **ሰርዓት/system/፡-** ማለት እርስበዕርሳቸው ግንኙነት ያላቸው ክፍሎች በሚፈጥሩት መስተጋብር ሙሉ ሆኖ የሚከናውን ነው፡፡
- በተቋም ውስጥ ሰራተኞች ስራን ለማከናወን ቴክኖሎጂን ይጠቀማሉ፤ መዋቅሩን በመጠቀም ደግሞ ጥምረት በመፍጠር የተለያዩ ተግባራትን በመከወን መሰረታዊ አገልግሎት ይሰጣሉ፡፡


- ሥርዓቱ ተቋሙን ከሰፊው አካባቢ ጋር ያለውን ማህበራዊ፣ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ግንኙነት ያመለክታል።
- ግንኙነቱ ክፍት ወይም ዝግ በሚል በሁለት መንገድ ይገለፃል። ማንኛውም ተቋም ሰርዓቱ/system/ ዝግ ከሆነ አይደለም የማህበረሰቡን ችግር ሊፈታ ቀርቶ እንደ ተቋም ሊቀጥል አይችልም።

- በአንፃሩ ሰርዓቱ ክፍት ከሆነ ተቋሙ ከአካባቢው በቁስ፣በሰራተኛ፣በአስተያየት፣በገንዘብ፣በሃሳብ መልክ ግብዓት ይፈልጋል።ማህበረሰቡ ደግሞ ከተቋሙ የአገልግሎቱ ተጠቃሚ ይሆናል በዚህም መልክ መመጋገቡ እስካለ ድረስ ተቋሙ ህያው ሆኖ በተግባሩ ተቀባይነት ይኖረዋል።
- በስራችን በኩል ከማህበረሰቡ ጋር ያለን ግንኙነት ዝግ ነው ወይስ ክፍት ነው ምን ይመስላል? ሚዛኑስ?

3. ተቋማዊ ቁርጠኝነት/ዝግጁነት/

- ተቋማዊ ቁርጠኝነት ማለት ተቋሙ ውጤታማ ይሆን ዘንድ በማንኛውም ፈታኝ ሁኔታ ውስጥ ሆነን ተግባራትን በማከናወን የተቋሙ ግቦች ስኬታማ እንዲሆኑ የምንደርገው መስተጋብር ነው።
- ከመደበኛ የስራ ሰዓት በተጨማሪ በመስራት ተሳትፏችንና ፍላጎታችን የሚገለፅበት ነው።

- አንድ ግለሰብ ተቀማጭ ቁርጠኝነቱን በአግባቡ ይወጣ ዘንድ የሚከተሉትን አለባቢያን በውስጡ ሊያዳብርና ሊሰንቅ ይገባ ዘንድ ወሳኝ ነው ይባላል፤


ስኬት
ቃልኪዳን
ተቋማዊ ቁርጠኝነት
መታመን
ውሳኔ
ስነምግባር
ብቃት

- በዚህም ከተቀመጥንለት ዓለማ ውጭ ለሚመጡ ለጊዜያዊ ጥቅሞች የማንታለል ዓለማ መርና ቁርጠኞች እንሆናለን።
- የምሰራው የሕግን ልዕልናን ላሰፍን እንጂ ወንጀለኛን ከህግ ሰይፍ ልታደግ አይደለም የማለት ወኔን መላበስ ነው።

- በጥቅም መቼም ሸብረክ አልልም፤ በሚመጣብኝ ጫና ወይም ጣልቃገብነት “በሀግ ፊት ሁሉም እኩል ነው” የሚለውን ህጋዊ መርህ በመሸራረፍ አልቀለበስም የማለት ህሊናዊ ቀለምን መለያ፤ የማንነት መታወቂያ ማድረግ የሃቅ ባለቤት የሆነ የህግ ባለሙያ መገለጫ ነው።
- በዚህ ልክ ተቋማዊ ቁርጠኝነታችንን ለመወጣት ግን ለህሊናችን በማደር ለስራችን የታመን መሆን አለብን።

3.1.በጎሊና መመራት

- ህሊና ማለት በእያንዳንዱ ሰው ውስጥ ያለ ግብረገባዊ ብይን ሰጭ ተቋም/moral faculty/ ነው።
- ሰዎች ካለባቸው ግዴታ አንፃር የድርጊቶችን ግብረገባዊ ወይም ኢግብረገባዊ ይዘት እንዲገመግሙ የሚያስችል ውስጣዊና መንፈሳዊ ህይወታቸው ነው።


Right
Wrong
?

- ህሊና ግብረገባዊ ሕግጋትን፣ብይንና መርህን የሚያገኘው ካለው ህብረተሰብ ነው።
- ከዚህ አንፃር ህሊና በግለሰብ ውስጥ ያለ የህብረተሰብ ድምፅ ወይም ተቋም ነው ማለት ይቻላል።
- እንደ ፍትህ አካል ፍትህ ለጠማው ወይም ለፍትህ ፈላጊው አብዛኛው የህብረተሰብ ክፍል በህሊናችን በመገዛት ምን ያህል ድምፅ መሆን ችለናል?

- በሳሊና ልዕልና መመራት ማለት ከራስ በላይ ለሀገርና ለሌሎች በሀሊናዊ ማንነት መኖር ነው፤ይህ በአብዛኛው ከተግባር ጋር የተገናኘ ነው።
- መልካም ነገርን መፈፀም የሚቻለው የራስን ደመነብስ ስሜት እና ፍላጎት በአዕምሮ በመቆጣጠር ነው።
- አዕምሮ በተባሉት ላይ የበላይነት መቀዳጀት የሚችለው በትምህርትና በምክንያት ሲበለፅግ ነው። ለዚህም ይረዳ ዘንደ አዕምሮ ሁሌ መመገብ አለበት።

- ሁሉንም ማገናዘብ የሚችል አእምሮ መሆን የሚገባውንና የማይገባውን አንጥሮ የሚያሳይ ብቻ ሳይሆን የሚገባውን ለመፈፀም፣የማይገባውን ለለመፈፀም ፈቃድ ሊኖረው ይገባል። ይህ የሚረጋገጠው በተግባር ሲፈተሽ ነው።
- ስለዚህ ህሊናዊ ልዕልና የዕውቀት እና የተግባር ውህደት ውጤት መገለጫ ነው።

- በዚህ አይነት ልበሙሉነት ለህሊና በመኖር ተቋማዊ ባህል መፍጠርና ማዳበር ይቻላል። እንደዛ ካልሆነ ከቆምንለት ዓለማ ውጭ ህሊናችን ተግባሩን ተነጥቋል/እንዲነጠቅ ሁኔታዎችን እያመቻቸን ነው/ ማለት ነው።
- ከሞት ቀድሞ የህሊና ሞት አለ፤ሕሊናው የሞተ ሠው ባይሞትም በድን ነው፤ከዚህ መሸሸ የንቁና የብቁ ዜጋ መለያ ነው።

- ባለንበት ሀገራዊ ተጨባጭ ሁኔታ አንፃር “ሰው፤ ሰው መሆንን መማር ያስፈልገዋል” አስተውሎቱን አጥቷልና።
- ምክንያቱ ደግሞ በህሊና የመመራት ዓቅሙን በጊዜያዊ ጥቅም እና በስሜታዊ እንቅስቃሴ ስለተነጠቀ ነው።
- ይህንን ትምህርት ከቤተሰብ፣ከሃይማኖት፣ከትምህርት ቤት፣ከታሪክ፣ከሳይንስና ጥበብ ማግኘት ካልተቻለ እንደ አራዊት በደመ-ነብስ እየተመራ መኖር ነው።

- “ሰብዓዊ ክብሩን ያጣ ሰውነቱን አጣ” ሰው ከእንስሳ የሚለየው በሰብዓዊ ክብሩ ነው። ሰብዓዊ ክብር በገንዘብ አይገዛም፤በሃይል አይዘረፍም፤ድህነትንና ባለሃብትነትን አያመለክትም፤የፖለቲካ ስልጣን ከመያዝና ካለመያዝ ጋር አይገናኝም በውስጣዊ እንጂ በአፋዊ ነገር አይመጣም።
- ስነ-ምግባርን ስንቅ ያደረገና ለህሊናው የሚኖር ሰብዓዊ ክብርን ይቀዳጃል።


Respect comes from self respect. If you respect yourself, people will respect you.
(Thoughts Wonder)

3.2. የምናገለግለው ህዝብ ምን ይለናል?

- በህዝባዊ ጫና በመንግስት በኩል “ለውጥ” በሚመጣ ጊዜ በመጠኑም ቢሆን የነባሩ **ሀጋዊ አካሄዶችና ተቋማዊ ጥንካሬዎች** ስለሚለሉ ሀገርና ህዝብ ለዘረፋ የሚዳረግበት እድል የሰፋ ነው። በአንፃሩ ህዝቡ ደግሞ ከነበረው የተሻለ መልካም ነገር ይፈልጋል።
- በዚህ ጊዜ ከተሰጣቸው ህዝባዊ ሃላፊነት አንፃር አዲስ **ስልት/ስትራቴጂ/ ቀይሰው** ካልተራመዱ በህዝቡ ልብ ውስጥ እያሉ የሉም የሚባሉ መንግስታዊ አካላት ይኖራሉ።

- መቼም እያለሀ የለሀም እንደመባል አዕምሯዊ እረፍት የሚነሳ ነገር የለምና ህዝቡ ሊያየውና ሊዳስሰው የሚችል ውጤታማ ስራ በመስራት አለሁ ማለት ተገቢ ነው።
- ለዚህም ይረዳ ዘንድ ይህንን የሚመጥን ከአካባቢው ተጨባጭ ሁኔታ በመነሳት የራስን ስልት ወይም ስትራቴጂ ነድፎ መንቀሳቀስ ሀጋዊና ሞራላዊ ግዴታ ነው።

- እንደ ፍትህ ተቋም መሪ ወይም ባለሙያ ምን ላይ ነን? በህዝቡ ዘንድ የተሰጠን እሳቤ ምንድነው?

- በምመራው ወይም በምሰራበት ተቋም ውስጥ ከለውጡ በፊት የነበሩ ህዝብን ያማረሩ ብልሹ አሰራሮች/ስርቆቶች/ አሉ ወይስ ተቀርፈዋል? ወደፊትስ እንዴት ነው መሄድ ያሰብነው?
- በማንኛውም የስራ ሃላፊነት/መደብ/ እስካለን ድረስ እንደግለሰብ ነገ በህይዎት ባልኖር ሰዎች/የምሰራበት ተቋም/ በምን መልካም ነገርና አሻራ ያስታዉሱኛል?

3.3. ተቋማዊ አመኔታን መፍጠር!

- በመልካም ስብዕና የታነፀ ሀዝባዊ አገልግሎት ሀዝባዊ አመኔታን ያጎናፅፋል።
- የምሰራው የተቋሙን ተልዕኮ በመፈፀም ተቋሙ ካስቀመጠው ራዕይ በመድረስ የህዝቡ ችግር እልባት እንዲያገኝ ነው በማለት ከልባቸው የሚታትሩ ሰራተኞች የማህበረሰቡን ትኩረት የመሳብ አቅማቸው ከፍተኛ ነው።

❖ በዚህም ተቋሙ ሰፊ ማህበራዊ መሰረት ይጥላል። “ስር ያለው ዛፍ አይወድቅም” ይባላልና ተቋሙም የዚህ ተጋሪ ይሆናል።

❖ትክክለኛ መሪና የሙያ ባለቤት ሃላፊነት የሚሰማውና ከራሱ አልፎ ለሚቀጥለው ትውልድ መልካም አሻራ ለማስቀመጥ አልሞ የሚሰራና የሚታትር ነው።

- ህዝብን ከሙስናና ከብዝበዛ ለማዳን፣ህይዎትን ለመጠበቅ፣ጥቅምን፣መብትና ክብርን ለማስጠበቅ ህግ በፍትህ አካላት በኩል ዋና አንቀሳቃሽ ሞተር በመሆን በመሳሪያነት ያገለግላል።

- በተመሳሳይ መልኩ የሕዝብ ፍላጎት ደግሞ ማህበራዊ ፍትህ በሰፈነበት ሁኔታ መኖር ነው። ለዚህም ይመስለል ማህበረሰባችን በረጂም የታሪክ ሂደቱ “ለህግ አምላክ” በመፍጠር መንፈሳዊነትን ያቀዳጀው። በኛ ዘመንስ ይህ የህግ መንፈሳዊነት አለ ወይስ ተራቁቷል?

- በስራ ሃላፊነታችን ህዝቡን ልናገለግል እስከተቀመጥን ድረስ የማህበረሰቡ ህመም የሚያመን፣ ችግሩ እረፍት የሚነሳንና ለችግሩ እስከቻልነው ድረስ መፍትሄ አፍላቂ እንጂ መሆን የሚጠበቅብን ችግሩን ታከን ሌላ ችግር ፈጣሪ መሆን የለብንም።
- ሰዎች ሕዝባቸውን በትክክል የራሳቸው ማድረግ የሚችሉት፤ ራሳቸውን ከልብ የሕዝባቸው ሲያደርጉ ነው።

- ፍትሀን ለማስፈን እስከሰራን ድረስ ከምናገለግለው ህዝብ ጋር ተቀራርበን ለመስራት የሚያግደን ነገር አይኖርም፤ ከፍ ያለ ቁርጠኝነትና የስራ ብቃት ማሳየት ግን የግንኙነቱ መልህቅ ይሆናል ማለት ነው።

- የሕዝብ አገልጋይ ማለት የሚመሩትንና የሚያገለግሉትን ህዝብ እንደ ሙስና ካሉ አስከፊ ጥፋቶች በመጠበቅ ራስን ለህዝብ ጥቅምና ክብር አሳልፎ መስጠት ስለሆነ ማለት ነው።

- በአዎንታዊም ሆነ በአሉታዊ ክንውኖች ማንኛውም ተቋም የመሪው ነፀብራቅ እንደሆነው ሁሉ ማንኛውም ሰራ ለሰሪው መስታውት ነው።
- የቆሙለትን ስራ በውጤት በማጀብ በሰሩት ስራ መኩራትና ፍትህን ማስፈን የትልቅ ሰብዕና መገለጫ ነው።

- አፍሪካን ከጫፍ እስከ ጫፍ አይቻለሁ፤በኢትዮጵያ አንድም ሌባ አላየሁም። ከፍተኛ የሃገር ሃብት ተመለከትኩ። እንዲህ ያለ ከፍተኛ ግብረገባዊ እሴትና አዋቂ ሕዝብ ያለባትን አገር በቅኝ ግዛትነት ማሸነፍ የምንችል አይመስለኝም። የምንችለው የአገሪቱ የጀርባ አጥንት የሆነውን መንፈሳዊና ባህላዊ ሃብቷን ስንሰባብር ብቻ ነው።




Thank you